ከአጋጣሚነት ወደመደበኛነት እየተለወጡ የመጡት ግጭቶች መንስዔ ምን ይሆን?

ኢብሳ ነመራ

የኃይማኖትና የብሄር ብዝሃነት ያላት ኢትዮጵያ ተቻችሎና ተከባብሮ የመኖር ምሣሌ ሆና ቆይታለች። በኢትዮጵያ ታሪክ ብሄርንም ይሁን ኃይማኖትን መነሻ ያደረገ የእርስ በርስ ግጭት አጋጥሞ አያውቅም። ብዝሃነትን ጨፍልቆ አንድ ብሄራዊ ማንነትና ኃይማኖት ያለው ኢትዮጵያዊነትን የመመሥረት ስትራቴጂ ይከተሉ የነበሩ የአሃዳዊ መንግሥት ሥርዓቶች በነበሩበት ወቅት እንኳን አንዱ ብሄር በሌላው ላይ አልተቆጣም፣ አልተነሳምም። በርካታ ብሄራዊ የነጻነት ንቅናቄዎች የትጥቅ ትግል ሲያካሂዱ በነበረበት እስከ 1983 ዓ.ም ድረስ በነበሩ ዓመታት፣ የነጻነት ንቅናቄዎቹ እንወክለዋለን ከሚሉት ውጭ የሆኑ ማኅበረሰቦች ላይ ጥቃት ሰንዝረው አያውቁም ወይም ጥቃት እንዲሰነዘር ህዝብን በህዝብ ላይ አነሳስተው አያውቁም። ከማንነት ባሻገር ለሰዎች መብትና ነጻነት መከበር ነበር የሚታገሉት። በትጥቅ ትግልም ሆነ በሌላ መንገድ ለመብትና ነጻነት ሲካሄዱ የነበሩ ትግሎች ህብረ ብሄራዊ ባህሪ የነበራቸው፣ የተለያየ ብሄርና ኃይማኖት አባላት በአንድ ግንባር ተሰልፈው የተዋደቁበት ሁኔታም ነበር። የብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች፣ የአመለካከትና የኃይማኖት እኩልነትና ነጻነት የተረጋገጠባት ዴሞክራሲያዊት ፌዴራላዊት ኢትዮጵያን መገንባት ያስቻለው መሠረት የተጣለው በእነዚህ ትግሎች የተገኘ ድል ነው።

ይሁን እንጂ የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች የራሳቸውን እድል በራሳቸው የመወሰን መብታቸው በህገ መንግሥት ተረጋግጦ ብሄራዊ መብታቸውና ነጻነታቸውን ማጣጣም ከጀመሩ በኋላ፤ በመካከላቸው እኩልነትና መከባበር መኖሩን ተገንዝበው በአገራቸው በማንነታቸው ተሸማቀው ከመኖር ተላቀው አንገታቸውን ቀና ካደረጉ  በኋላ ግጭቶች መታየት ጀምረዋል። የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች በሚኖሩበት መልከዓምድራዊ ወሰን ውስጥ በቋንቋቸው እየሰሩ፣ ልጆቻቸውን በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው እያስተማሩ፣ ባህላቸውን እያስተዋወቁና እያጎለበቱ፣ እውነተኛ ታሪካቸውን እያጠኑና እየተንከባከቡ የመኖር መብታቸው ተረጋግጦ የጋራ ጉዳያቸውን ደግሞ ሁሉም በተወከሉበት የፌዴራል መንግሥት በሚያስተዳድሩበት ሥርዓት የእርስ በርስ ግጭት እንዲቀሰቀስ የሚያደርግ ተጨባጭ ነባራዊ ሁኔታ የለም። በፌዴራላዊ ሥርዓቱ የሚነሱ ግጭቶች ከነባራዊ ሁኔታና ከመርህ አኳያ ሲታዩ ከሚጠበቀው ተቃራኒና መሆን ያልነበረባቸው ናቸው።

መሆን ያልነበራቸው ቢሆኑም የሆኑበትን አጋጣሚ ግን ተመልክተናል። የብሄር መልክ ያለው ግጭት እንዲያውም ከጊዜ ወደጊዜ እየሰፋ የመጣበት ሁኔታ ነው የሚታየው። ይህ  ከነባራዊ ሁኔታና ከመርህ ያፈነገጠው ግጭት ውጪያዊ መንስዔ ወይም ገፊ ኃይል ያለው መሆኑን ያመለክታል።

በዚህ ጉዳይ ላይ ግልጽ እይታ እንዲኖረን በአገራችን ባለፉት ሦስት ወራት ገደማ የነበረውን ሁኔታ ብቻ መለስ ብለን እንመልከት። አነሳሱ ቀደም ያለ ቢሆንም በኦሮሚያና በኢትዮጵያ ሶማሌ አዋሣኝ አካባቢዎች ከያዝነው ዓመት መግቢያ ጀምሮ በኦሮሞዎችና በኢትዮጵያ ሶማሌ ተወላጆች መካከል ግጭቶች የሚካሄዱበት ሁኔታ አለ። በሁለቱም ወገን በመቶ ሺህ የሚቆጠሩ ዜጎች ተፈናቅለዋል። የሞቱና የቆሰሉም አሉ። ግጭቱ አሁንም አላባራም። ሰሞኑን በምሥራቅ ሐረርጌ ጨለንቆ እንዲሁም በምዕራብ ሐረርጌ ዳሩ ለቡ እና ሃዊ ጉዲና በተባሉ ወረዳዎች ለበርካታ ኦሮሞዎችና ሶማሌዎች ሞት ምክንያት የሆነ አስከፊና አሳዛኝ ግጭት ተቀስቅሷል። ይህ በኢትዮጵያ ሶማሌ ክልልና በኦሮሚያ አዋሣኝ አካባቢዎች ያጋጠመ ሁከት ራሱን የቻለ ሰፊ አጀንዳ ስለሆነ ዝርዝሩን በሌላ ጽሁፍ የምመለስበት ይሆናል። ይሁን እንጂ ለዘመናት በሠላም አብረው ይኖሩ በነበሩ ብሄሮች መካከል የተፈጠረ ግጭት መሆኑ ሊያዝ ይገባል።

ከዚህ ከግዙፉ ግጭት በተጨማሪ ባለፉት ሦስት ወራት የብሄር ገጽታ ያላቸው በርካታ ጥቃቅን ግጭቶች እዚህም እዚያም አጋጥመዋል። በኦሮሚያ ቡኖ በደሌ ዞን ሦስት ወረዳዎች በኦሮሞና በአማራ ተወላጆች መካከል ለሰዎች ህይወት መጥፋት ምክንያት የሆነ ግጭት አጋጥሟል። በዚሁ ሰሞን በምሥራቅ ወለጋ ዞን ነቀምቴ ከተማ የኢሬቻ በዓል ላይ ሁለት ግለሰቦች ላይ ብሄርን መሠረት ያደረገ ጥቃት ተፈጽሟል። በኦሮሚያ ምዕራብ አርሲ ዞን ባቱ (ዝዋይ) ከተማ አካባቢ የሁለት ግለሰቦችን ግጭት መነሻ ያደረገ በኦሮሞዎችና በወላይታ ተወላጆች መካከል ጎራ የለየ የቡድን ግጭት አጋጥሟል። በዚሁ በምዕራብ አርሲ ዞን አርሲ ነገሌ ከተማ የመጠጥ ግሮሰሪ ውስጥ በግሮሰሪው ባለቤትና ደንበኛ መካከል  የተፈጠረና ለአንድ ገላጋይ ህይወት ህልፈት ምክንያት የሆነ ግጭት፣ በማግስቱ ጠዋት የኦሮሞና የአማራ ተወላጆች ግጭት የሚመስል ባህሪ ይዞ እንደነበረ ይታወሳል። በደቡብ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ደቡብ ኦሞ ዞን በአንድ የአካባቢው ተወላጅ ሴት ላይ የመኪና አደጋ መድረሱን ተከትሎ ከሌላ አካባቢ የመጡ ኢትዮጵያውያን ላይ ለሰው ህይወት መጥፋት ምክንያት የሆነ ጥቃት ተፈጽሟል።

እነዚህ ብቻ አይደሉም። በህዳር ወር ማብቂያ ላይ በአማራ ክልላዊ መንግሥት ሰሜን ወሎ ዞን በወልዲያ ከተማ፣ በመቀሌና ወልዲያ ከተማ የእግር ኳስ ቡድኖች መካከል ሊካሄድ የነበረን ግጥሚያ መነሻ በማድረግ ጨዋታው ከመጀመሩ ከሰዓታት አስቀድሞ በተፈጠረ ትንኮሳ ብሄርን መሠረት ያደረገ ግጭት ተቀስቅሶ ለሁለት ሰዎች ሞት ምክንያት ሆኗል። ይህን ተከትሎ በትግራይ ክልል አዲግራት ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ብሄርን መሠረት ባደረገ ግጭት የአንድ ሰው ህይወት አልፏል። ከዚሁ ጋር ተያይዞ በኦሮሚያ ሆሩ ጎድሩ ወለጋ ዞን በወለጋ ዩኒቨርሲቲ ነጆ ካምፓስ በተቀሰቀሰ ብሄርን መሠረት ያደረገ ግጭት ሁለት ተማሪዎች ተገድለዋል።

እነዚህ ወትሮ በአገሪቱ ከነበረው ሁኔታ በተለየ በተከታታይ ያጋጠሙ የአብዛኛቹ ግጭቶች መነሻቸው ከብሄራዊ ማንነት ጥያቄ ጋር ምንም ዝምድና የሌላቸው ናቸው። አብዛኞቹ ጊዜያዊ የግለሰቦች ፀብን፣ የእግር ኳስ ደጋፊነትን እንዲሁም የአጋጣሚ አደጋን መነሻ ያደረጉ ናቸው። ይሁን እንጂ ሁሉም የብሄር ገጽታ ይዘዋል ወይም እንዲይዙ ለማድረግ ተሞክሯል። ይህ ሁኔታ ከላይ የጠቀስኳቸውን በተለያየ ሥፍራ

በተለያየ መነሻ ምክንያት ያጋጠሙ ግጭቶች ተመሳሳይ ያደርጋቸዋል። የተለያየ መነሻ ኖሯቸው ተመሳሳይ መልክ እንዲይዙ መደረጉ ግጭቶቹን የቃኛቸው አካል አንድ ወይም ተዛማጅነት ያላቸው መሆናቸውን ያመለክታል።

ይህን ሁኔታ ሰፋ አድርገን ስንመለከተው ኢትዮጵያ ውስጥ ማንኛውንም ግጭት አመቺ ሆኖ ከተገኘ የቡድን - የብሄር ወይም የኃይማኖት ገጽታ በመስጠት ለማዛመትና አገሪቱን ለማተራመስ ተዘጋጅቶ የተቀመጠ ሥልት መኖሩን ያመለክታል። ከዚህ ሥልት ጀርባ ደግሞ ሥልቱን የነደፉና የሚያስፈጽሙ አካላት አሉ።

እነዚህ አካላት ኢትዮጵያን በእርስ በርስ ግጭት በማተራመስ ዳግም አገር መሆን በማትችልበት ሁኔታ የማፈራረስ ስትራቴጂ የሚከተሉ አካላት መሆናቸውን መገመት ብዙም ምርምር የሚጠይቅ አይደለም። ከእነዚህ የአገሪቱ ስትራቴጂካዊ ጠላቶች ጋር የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ነን ብለው በአሜሪካና በኤርትራ የመሸጉ ቡድኖችም ተሰልፈዋል። እንዲያውም ዋነኞቹ የስትራቴጂው አስፈጻሚዎች እነዚህ አካላት ናቸው። እነዚህ የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ነን የሚሉ አገሪቱን የማተራመስ የጠላት ስትራቴጂ አስፈጻሚዎች የሚጠቀሙባቸው የማህበራዊ ሚዲያዎች ጥቃቅን ግጭቶችን ተቀጣጣይ ወደሆኑ የብሄር ግጭትነት እንዲሸጋገሩ በማድረግ ረገድ ትልቅ ሚና ተጫውተዋል። ዘሐበሻ፣ መረጃ ዶት ኮም፣ ዲጂ ኢትዮጵያ . . . የመሳሰሉ የኤርትራ መንግሥት የሚመራቸውና እነ ግንቦት 7 የሚጠቀሙባቸው ማህበራዊ ሚዲያዎች ጥላቻ በመቀስቀስ፣ ግጭቶች የብሄር መልክ እንዲይዙና እንዲስፋፉ በማድረግ ረገድ ትልቅ ድርሻ መወጣታቸውን ልብ ይሏል።

ለዚህ አስረጂነት አንድ ምሣሌ ልጥቀስ። በአዲግራት ዩኒቨርሲቲ ለአንድ ተማሪ ህይወት መጥፋት ምክንያት የሆነው ግጭት መቀስቀሱን ተከትሎ፣ ዘሃበሻ የተባለው የፌስ ቡክ ገጽ በግጭቱ ሰባት የአማራ፣ ሰባት የኦሮሞ፣ አንድ የደቡብ ብሄሮች ተወላጆች የሞቱ አስመስሎ በድምሩ የ15 ሰዎችን ስም ዝርዝር አስፍሮ ነበር። እውነታው ግን ፍጹም ከዚህ የተለየ ነበር። በግጭቱ የሞተው አንድ ተማሪ ብቻ ነው። የአንድ ተማሪ መሞት ዋጋ አይሰጠውም እያልኩ እንዳልሆነ ግን ልብ በሉ። የኤርትራ መንግሥት ኢትዮጵያን በእርስ በርስ ግጭት የማጥፋት ስትራቴጂ አስፈጻሚ የሆኑ ቡድኖች የሚጠቀሙበት ዘሐበሻ የተሰኘው ድረ ገጽና የፌስ ቡክ ገጽ ይህን ዓይን ያወጣ ውሸት ያሰፈረው የተሳሳተ መረጃ ደርሶት አይደለም። አስቦና አልሞ፣ የሚያስከትለውን ውጤት አውቆና ፈልጎ ነው ሐሰተኛውን መረጃ ያሰራጨው። ዓላማውም በኦሮሚያና በአማራ ክልሎች የሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ በትግራይ ተወላጅ ተማሪዎች ላይ ጥቃት እንዲሰነዘር ለማነሳሳት፣ ከተቻለም ይህን ግጭት ወደተቀረው ኅብረተሰብ በማዛመት አገሪቱን ለማተራመስ ነው። ዘሐበሻና ቢጤዎቹ ከላይ ከጠቀስኳቸው የግለሰብ ፀብን ወይም ሌላ ምክንያትን መነሻ በማድረግ የተቀሰቀሱ ግጭቶችን አስመልክቶ ያሰራጫቸውን መረጃዎች በሙሉ ብትመለከቱ ይህን እውነታ በግልጽ መረዳት ትችላላችሁ።

እርግጥ ነው የክልል መንግሥታትም ሆነ የፌዴራል መንግሥት ግጭቶች እንዳይቀሰቀሱ በቂ የፖለቲካ ሥራ ያልሰሩበት ሁኔታ አለ። ግጭቶች ካጋጠሙ በኋላም እንዳይባባሱና በሌላ ሥፍራ ተመሳሳይ ግጭት እንዳይፈጠር ለማድረግ በቂ የፖለቲካ ሥራ ያልተከናወነበት ሁኔታም ተስተውሏል። ፈጣን የህግ ርምጃዎች አለመወሰዳቸው፣ የግጭቶችን ተጽዕኖ ለመቀነስና በአጠቃላይ በግጭቶቹ ዙሪያ የሚሰሩ የኮሚዩኒሽን ሥራዎች የሚወሰዱ ግጭት ቀስቃሽ ሁኔታዎችን ያመቻቹበትን ሁኔታም ታዝበናል።

ያም ሆነ ይህ፤ ግጭቶች ከጊዜ ወደ ጊዜ  የተለመዱ እየሆነ መምጣት፣ ማንኛውም ዓይነት መነሻ ያለው ግጭት የብሄር መልክ የሚይይዝበት ሁኔታ መደጋገም ድንገተኛ ክስተት አይደለም። ከዚህ ይልቅ ሆን ተብሎ አገሪቱን ለማተራመስ በወጡኑ አካላት የሚሰራና የሚመራ ነው። በመሠረቱ ፌዴራላዊ ሥርዓቱ በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ እኩልነትና መከባበርን በማስፈን የእርስ በርስ ግጭቶች እንዳይፈጠሩ የግጭት ምክንያቶች ሊሆኑ የሚችሉ ሁኔታዎችን የሚያስወግድ ነው። ፌዴራላዊ ሥርዓቱ በፍጹም የግጭት ምክንያት ሊሆን አይችልም። ፌዴራላዊ ሥርዓቱ በክልሎች ወይም በብሄሮች መካከል አለመግባባቶች ቢያጋጥሙ እንኳን ወደግጭት ወይም የኃይል መፍትሄ ሳይገባ በሠላማዊ መንገድ መፍታት የሚያስችል ህገ መንግሥታዊ የመፍትሄ ድንጋጌዎች አሉት።

እርግጥ ነው፣ ከዚህ ህገ መንግሥታዊ ሥርዓት አፈጻፀም መጓተት ግጭቶች እንዲቀሰቀሱ ማድረግ የሚያስችል አመቺ ሁኔታ መፈጠሩ አይካድም። ይሁን እንጂ ግጭቱን የሚመሩት ቡድኖች የግጭቱን መንስዔ ፌዴራላዊ ሥርዓቱ አስመስለው በማቅረብ ለሌላ ሰፊ ግጭት እየተዘጋጁም መሆኑንም የኢትዮጵያ ህዝብ ሊገነዘብ ይገባል። በአጠቃላይ በአገሪቱ እያጋጠሙ የሚገኙት የብሄር መልክ ያላቸው ግጭቶች እንዲቀሰቀሱ በማድረግ ረገድ የመንግሥት የህገ መንግሥት አፈጻፀምና ያለመግባባቶች የተያዙበት መንገድ ክፍተት መፍጠራቸው ባይካድም በዋናነት የሚመሩትና እንዲዛመቱ የሚደረጉት ግን በኢትዮጵያ ስትራቴጂካዊ ጠላቶችና ተላላኪዎቻቸው መሆኑን ማስታወስ ቢያንስ ሊሆን እንደሚችል መገመት ብልህነት ነው።